# Francis C. Hammond Middle School
## Parent and Family Engagement Policy
## 2025-2026

የፍራንሲስ ሲ. ሃመንድ (Francis C. Hammond) መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፤ በተማሪዎች የቀለም-ትምህርት ስኬታማነት ላይ፣ የወላጅ ተሣትፎ - ወሳኝ-ሚና መኖሩን ከፍተኛ-ዋጋ የሚሰጠው ነው። ፍራንሲስ ሲ. ሃመንድ (Francis C. Hammond) MS፤ የወላጆች ተሳትፎ ማድረግ-ማለት፣ ወላጆች በመደበኛነት በሁለት-በኩል የሆነ፣ እና የተማሪዎችን የቀለም ትምህርትን እና ሌሎች የትምህርት ቤት እንቅስቃሴዎችን ያካተተ - ትርጉም-ሰጪ ግንኙነት የያዘ መሆኑን ያምናል፤ ይኸውም የሚከተሉትን በማረጋገጥ-ላይ ያከተተም ይሆናል:

1. በልጆቻቸው መማር ላይ እገዛ ለማድረግ፣ ወላጆች ዋነኛውን ሚና ይጫወታሉ
2. በትምህርት ቤት ውስጥ፣ በልጆቻቸው የትምህርት ጉዳይ ላይ፤ ወላጆች የነቃ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ይበረታታሉ
3. በልጆቻቸው የትምህርት ጉዳይ ላይ፣ ወላጆች ሙሉ-አጋሮች በመሆን እና እንደ-ተገቢነታቸው - በውሳኔ አሰጣጥ እና በልጆቻቸው ትምህርት ላይ እገዛ ለማድረግ በአማካሪ ኮሚቴዎች ውስጥ ይካተታሉ

<u>የዕቅድ አወጣጥ፣ ሂደት</u>

የፍራንሲስ ሲ. ሃመንድ (Francis C. Hammond) መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፤ ከትምህርት ቤት ሠራተኞች፣ ማህበረሰብ አባላቶች፣ እና ወላጆች ጋር በመመካከር፣ ይህን የወላጅ ተሳትፎ ፖሊሲን በጋራ የቀረጸ ሲሆን፣ እና በኖቬምበር (November) 8 ቀን 2017፣ በስራ-ላይ አውሏል። ፖሊሲው፤ በኦክቶበር **(October) 16** ቀን **2025** ላይ፣ እንደገና አዲስና-ማስተካከያ/updated የሚደረግለት ይሆናል።

ይህ ፖሊሲ፤ ለወላጆች ተሰራጭቶ የነበረ እና በተቻለ ተግባራዊ በሚሆንበት ሁኔታ፣ ወላጆች በሚረዱት ቋንቋ እንዲቀርብ ተደርጓል። ይህ ፖሊሲ፤ በትምህርት ቤቱ ድህረ-ገጽ፣ በኢሜል እና በበራሪ-ወረቀት (newsletter) ላይ ተገኝቶ፣ ለወላጆች እና ለአካባቢው ህብረተሰብ እንዲዳረስ ይደረጋል። የወላጅ እና ቤተሰብ ተሳትፎ ፖሊሲ፣ በዓመታዊው የ'Title I' ስብሰባ - በሴፕቴምበር **(Sept.) 18** ቀን **2025** ላይ፣ የሚጋራ-ይሆናል። ለወላጆች፣ የTitle I ዕቅድ (ማመልከቻ) አጥጋቢ ካልሆነላቸው፤ የ [local educational agency]፣ ዕቅዱን ለስቴቱ ሲያስገባ፣ ከማመልከቻው ጋር - የማንኛውንም ወላጅ አስተያየቶች አብሮ ያስገባል። የወላጆች ተሳትፎ እቅድ፣ የወላጆችን እና የትምህርት ቤትን - ተለዋዋጭ የሆነ ፍላጎቶችን ለማሟላት፣ በየዓመቱ አዲስና ማሻሻያ (updated) ያደርጋል።

<u>ትምህርት ቤት እና ቤተሰብ - ጥምረት **(COMPACT)**</u>

የፍራንሲስ ሲ. ሃመንድ (Francis C. Hammond) መካከለኛ-ደረጃ/Middle ትምህርት ቤት እና በትምህርት ቤቱ ውስጥ የሚማሩ-ተማሪዎች ወላጆች፤ ይህ የጥምረት ዝርዝሮች (compact outlines)፣ ወላጆች፣ አጠቃላይ ትምህርት ቤት ሠራተኞች፣ እና ተማሪዎች - የተማሪውን የቀለም ትምህርት ስኬትማነት ለማሻሻል እና፣ ትምህርት ቤት እና ወላጆች - ልጆች የስቴቱን ከፍተኛ ደረጃዎች/high standardsን እንዲያገኙ በሚረዳቸው ነገሮች ላይ ለመገንባት እና አጋርነትን ለማሳደግ፣ ያላቸውን ኃላፊነት እንዴት እንደሚያጋሩ ይዘረዝራል። ይህ የትምህርት ቤት-ወላጅ ጥምረት (compact)፤ ለትምህርት ዓመት 2025-2026 በስራ ላይ ውሎ-የሚያገለግል ነው።

<u>የትምህርት ቤት ስምምነት</u>

የፍራንሲስ ሲ. ሃመንድ **(Francis C. Hammond)** መካከለኛ **(Middle)** ደረጃ ትምህርት ቤት የሚከተሉትን ያደርጋል:

- ከፍተኛ ጥራት ያለው ስርዓተ-ትምህርት እና የትምህርት አሰጣጥን፤ ድጋፍ-ሰጪና ውጤታማ የመማሪያ አካባቢ ውስጥ - ተሳታፊ ተማሪዎች የስቴቱን የትምህርት ብቃት ደረጃን እንዲያሟሉ ለማስቻል፣ የሚከተሉትን ያከናውናል:
    - በመማሪያ-ክፍል ውስጥ፣ የሚያበረታታ እና ፍላጎትን-የሚጨምር የመማር ልምዶችን ማቅረብ፣
    - ስርዓተ ትምህርቱን የሚደግፍ፤ ለእያንዳንዱ ተማሪ ተስማሚ-ሆኖ የሚሰሩትን ቴክኒኮች እና ቁሳቁሶች ለመጠቀም እና ለመወሰን፣
    - ለተማሪዎቻችን፣ የሚጠበቅባቸውን ከፍተኛ-ድረጃ ያለውን መማር እንዲጠብቁ ማድረግ፣

- ከወላጆች ጋር አጋርነትን-በመፍጠር፣ ልጆቻቸውን በትምህርታቸው ላይ ለመርዳት የሚችሉበትን መንገዶች፤ እንደ - በትምህርት ገበታ መገኘትን መቆጣጠር፣ ማንበብና መፃፍ፣ እና የቴክኖሎጂ ስልጠናን፣ እንደ አስፈላጊነቱ፤  የወላጆች ተሳትፎን ለማስፋፋት፣ ከልጆቻቸው ትምህርት ጋር ግንኙነት ያላቸውን ውሳኔዎች ውስጥ ለመካፈል እንዲችሉ እና ከትምህርት ቤት ውጪ ያሉ እንቅስቃሴዎች (extracurricular) ላይ ያላቸውን ጊዜ በመጠቀም ላይ አዎንታዊ-በሆነ መልኩ እንዲጠቀሙ የሚያስችላቸውን መንገዶች ያቀርባል።
-

- ዓመታዊ ስብሰባ ማካሄድ ተካፋይ ለሆኑ ልጆች ወላጆች - አመቺ የሆነውን ጊዜ መርጦ፣ የትምህርት ቤታቸውን በ'Title I' ውስጥ መካፈልን፣ የ'Title I' መስፈርቶችን፣ እና ለመካፈል ወላጆች ስለአላቸው መብቶች፤ ለወላጆች ለማሳወቅ ማካሄድ። የዚህ-ዓመት፣ የ'Title I' ምሽት፣ ሴፕቴምበር **(September) 18** ቀን **2025** ላይ እንዲካሄድ - የጊዜ-ሰሌዳ ተይዞለታል። ሁሉም ወላጆች የተጋበዙ እና እንዲሳተፉም ይበረታታሉ።

- ተለዋዋጭነት-ያለው/**flexible** የስብሰባ ሰዓቶችን መስጠት፤ እንደ - ስብሰባዎችን በጠዋት-ጊዜያቶች ላይ ወይም ከሰዓት-በኋላ ምሽት-ላይ ባሉ-ጊዜያት ማድረግ፣ እና በዙም/Zoom እና በአካል-ተገኝቶ (in person) ድብልቅ-የሆነ/hybrid የስብሰባዎች አማራጭ-ማቅረብ።

- የወላጅ-አስተማሪ ስብሰባዎችን **-** በዓመት ሁለት-ጊዜ ማካሄድ፤ በዚህ ጥምረት **(compact)** ወቅትም፤ ከእያንዳንዱ ልጅ የግል ስኬታማነት ጋር በተያያዘ ሁኔታ ውይይት ይደረጋል።
  - የወላጅ-አስተማሪ ኮንፈረንሶች፣ ኦክቶበር **(October) 13** ቀን **2025**፣ እና ፌብሩዋሪ **(February) 25** ቀን **2026**፣ ይካሄዳሉ።
  - ስጋት ወይም አስፈላጊነት እንዳለው፣ ወላጅ ወይም አስተማሪ እንዲደረግ ከጠየቁ፤ ኮንፈረንሶቹ በማንኛውም ጊዜ ሊካሄዱ ይችላሉ።

- ስለልጆቻቸው የእድገት ሂደቶች፤ በየጊዜው ሪፖርቶችን ለወላጆች ማቅረብ። በተለይ-ደግሞ፣ ትምህርት ቤቱ በሚከተለው-ሁኔታ ሪፖርቶችን ያቀርባል**:**
  - በእያንዳንዱ የቀለም ትምህርት አጋማሽ (academic quarter) መጨረሻ ላይ፣  ሪፖርት ካርድ ወደ ቤት ይላካል። ከሚከተሉት አጋማሽ (quarter) መጨረሻ ቀናቶች በኋላ፣ ሪፖርት ካርዶች ወደ መኖሪያ-ቤት ይላካሉ:  ኖቬምበር **(November) 4**፣ ጄንዋሪ **(January) 26**፣ ኤፕሪል **(April) 6** ቀን፣ እና ጁን **(June) 12** ቀን።
  - ወላጆች፤ በኢሜል፣ ቴክስት (text) መልዕክቶች፣ እና/ወይም በስልክ ጥሪ አማካኝነት፣ የልጆቻቸውን የእድገት ሂደቶችን የሚያሳዩ ሪፖርቶች እንዲሰጣቸው ጥያቄ ባቀርቡ ጊዜም፣ ይሠጣቸዋል።

- በትምህርት ቤቱ የ**'Title I'** ፕሮግራም፤ ዕቅድ አወጣጥ፣ ምልከታ፣ እና ማሻሻያ ላይ፤ ወላጆችን በተቀናጀ፣ በቀጣይነት፣ እና ጊዜውን በጠበቀ መንገድ ማሳተፍ።
  - በ'CSIP' እና 'Title I' በጀት ላይ፣ ሁሉም-ወላጆች አስተያየት-ለመስጠት  እንዲችሉ፣ የዳሰሳ-ጥናት (survey) የሚቀረጽ እና የሚላክ-ይሆናል። (በኤፕሪል/April 2026 ይላካል)
  - በ'ዓመታዊው የ'Title I' ስብሰባ' ላይ፣ ሁሉም-ወላጆች አስተያየት-ለመስጠት  እንዲችሉ፣ የዳሰሳ-ጥናት (survey) የሚቀረጽ እና የሚላክ-ይሆናል። (በሴፕቴምበር /September 2025 ተልኳል)

- የእንግሊዘኛ-ቋንቋን የሚማሩ-ተማሪዎች ላሏቸው ወላጆች፤ ውጤታማ የሆነ ሁሉን-የማዳረስ **(outreach)** ዘዴዎች እንዲተገበሩ በማድረግ፤  ወላጆች በሚገባቸው ቋንቋ፣ የሚከተሉትን እንዴት ማከናወን እንደሚችሉ ለማስረዳት—
  - በልጆቻቸው የትምህርት አሰጣጥ ላይ እንዲካፈሉ፤ እና
  - ልጆቻቸውን፣ በሚከተለው እርዳታ በማድረግ ላይ ንቁ ተሳታፊዎች እንዲሆኑ—

- ○ የእንግሊዘኛ-ቋንቋ የላቀ-የብቃት ደረጃ/English proficiencyን ማግኘት፤
- ○ ብዙ ነገሮችን የሚሸፍን የትምህርት አሰጣጥ (well-rounded education) ውስጥ ከፍተኛ ደረጃዎችን ለማግኘት፤ እና
- ○ ሁሉም ተማሪዎች እንዲወስዱ የሚጠበቅባቸው የ'State academic standards' መሰናክሎችን ሚሟላት እንዲችሉ

- ለምሳሌ:
    - በሁሉም-ስብሰባዎች ላይ፣ የማስተርጎም አገልግሎት ይኖራል
    - ወደ ወላጆች የሚላኩ መረጃዎች - ይተረጎማሉ
    - የ'EL' ተማሪዎች፤ ወላጆች ስለ'EL' ፕሮግራም፣ ACCESS for ELLs ግምገማ/፣ እና ማመቻቻዎች፣ ወዘተ...፣ ለ'EL' ተማሪዎች በ'SOL' ግምገማዎች ላይ ለመወያየት ልዩ ስብሰባዎች ይካሄዳሉ።
    - ወላጆች፤ በልጃቸው ትምህርት-ላይ እንዴት እንደሚሳተፉ እና የእንግሊዘኛ-ቋንቋ በብቃት-እንዲያውቁ የሚያስችላቸውን - መረጃዎች፣ ተሰጥቷቸዋል።

<u>የርዕሰ መምህሩ/የአስተዳደራዊ ቡድን ስምምነት</u>

የፍራንሲስ ሲ. ሃመንድ **(Francis C. Hammond)** መካከለኛ **(Middle)** ትምህርት ቤት፣ ርዕሰ መምህር/ አስተዳደራዊ ቡድን፣ የሚከተሉትን ያደርጋሉ:

- የቤተሰብ ተሣትፎ ፖሊሲ (Family Involvement Policy)ን፣ ማጎልበት እና አፈፃፀሙን መደገፍ።
- ለመማር ሂደቱ፣ መልካም የሆነ አካባቢን እንዲኖር ማጎልበት።
- በአስተማሪዎች፣ ወላጆች እና ተማሪዎች መካከል ግንኙነትን-ለማድረግ የሚያስችሉትን-ሁኔታዎችን ማጎልበት።
- የትምህርት እንቃስቃሴዎች፣ ኮሚቴዎችን እና ፕሮግራሞችን መደገፍ እና መካፈል።

<u>የትምህርት ቤት ሠራተኞች - ስምምነት</u>

የፍራንሲስ ሲ. ሃመንድ **(FRANCIS C. HAMMOND)** መካከለኛ **(MIDDLE)** ደረጃ ትምህርት ቤት - ሠራተኞች፣ የሚከተሉትን ያደርጋሉ:

- ልጅዎ ለመማር ሂደቱ ኃላፊነትን ሊወስድ የሚችልበትን፣ እንክብካቤ የተሞላበትን የመማሪያ አካባቢን ማቅረብ።
- ለቤተሰቦች አመቺ የሆነ መልካም መስተንግዶ የሚያገኙበትን ሁኔታ ማጎልበት።
- የትምህርት ቤት እንቅስቃሴዎችን መደገፍ እና መሳተፍ።
- ከACPS የስርዓተ-ትምህርት እና የስቴቱ መስፈርት (State Standards) ጋር የሚጣጣም የበለፀገ እና የበለጠ-እንዲሰሩ የሚያደርጋቸውን - ስርዓተ-ትምህርት ማቅረብ።
- ጤናማ፣ ማህበራዊ እና ስሜታዊ የመማር ሂደትን ሊያጎለብት የሚችል፣ ተንከባካቢ የመማሪያ አካባቢን ማቅረብ።
- የኮሌጅን እና የስራ-መስክ ዝግጁነትን ለማበረታታት የሚችል አካባቢን ማጎልበት።

<u>የወላጅ/የአሳዳጊ ስምምነት</u>

የፍራንሲስ ሲ. ሃመንድ **(Francis C. Hammond)** መካከለኛ **(Middle)** ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች የሚከተሉትን ያደርጋሉ:

- በሰዓቱ፣ በመደበኛነት የትምህርት-ገበታ ላይ መገኘትን፣ አጽንዖት ይሰጣል።
- ስለልጆቻቸው የየቀኑ የትምህርት ውሎ እና ምን እንደተማሩ መጠይቅ።
- ሁሉንም የቤት/የክፍል ስራዎች (assignments) በጊዜው ማጠናቀቅን፣ አጽንዖት ይሰጣል።
- በ'Parent Square'፣ በወላጆች- አስተማሪ ኮንፈራንሶች፣ እና/ወይም በ'PowerSchool' እና ካንቫስ (Canvas) ላይ በሚደረጉ አዲስና ማሻሻያዎች (updates) አማካኝነት፤ መደበኛ የትምህርት ቤት ግንኙነቶችን መጠበቅ።
- በእያንዳንዱ ዓመት፣ ቢያንስ በአንድ የትምህርት ቤት ዝግጅት ውስጥ ለመካፈል ጥረት ማድረግ (ማለትም፤ በPTA፣ በ'Back To School' ምሽት፣ የትምህርት ቤት ኮንሰርቶች፣ የወላጅ ቡና/Parent Coffees፣ የSTEM ምሽት፣ የማንባበና-መፃፍ ምሽት/Literacy Night፣ ወዘተ...)

<u>የተማሪ ስምምነት</u>

የፍራንሲስ ሲ. ሃመንድ **(Francis C. Hammond)** መካከለኛ **(Middle)** ደረጃ ትምህርት ቤት፤ ተማሪዎች፣ የሚከተሉትን ያደርጋሉ:

- ትምህርት ቤት በመደበኛነት ተገኝቶ መማር እና በሰዓቱ መገኘት።
- በየትምህርት ዓይነት በየክፍል ትምህርት ምን እንደሚጠበቅ፣ ማወቅ።
- የአድሚራል ፕራይድ (Admiral Pride)ን ለማሳየት መጣር።
- ስለሚማሩት ነገሮች፣ ጥያቄዎችን መጠይቅ እና ለማወቅ-ጉጉት ማሳደር።
- በመማር-ሂደታቸው ውስጥ እና የቤት/የክፍል ስራዎችን (assignments) በሙሉ መጠናቀቁን በመከታተል፣ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ።

- ወደ ትምህርት ቤት ሲመጡ፣ ለመማር ተዘጋጅተው መምጣት - አስፈላጊ-ከሆኑ የመማሪያ ዕቃዎች ጋር መምጣት እና/ወይም የመማሪያ ዕቃዎች ሲያስፈልጓቸው ለራሳቸው ተከራካሪ-ሆነው መቆንም እንዲማሩ (ለምሳሌ: ክሮም-ቡክ (Chromebook)፣ አጀንዳ ደብተሮች (Agenda Books) እስክሪብቶዎች፣ እርሳሶች፣ ማስታወሻ-ደብተሮች፣ ባይንደሮች (Binders)፣ ወዘተ...)